የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ.ህ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No. 14
ADDIS ABABA 5th February, 2008

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ.ህ ዓ.ም

ለአሳታፊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፲፪

Proclamation No. 563/2008

International Fund for Agricultural Development Programme Financing Agreement for Participatory Small–Scale Irrigation Development Programme Ratification Proclamation Page 4012

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ.ህ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአሳታፊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፫ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር /አሥራ ሦስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፰ ቀን ፪ሺ.ህ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «ለአሳታፊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፫/፪ሺ.ህ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 563/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL FUND FOR AGRICUTURAL DEVELOPMENT

**WHEREAS,** a Programme Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development stipulating that the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 13,300,000 (thirteen million three hundred thousand Special Drawing Rights) for financing participatory small–scale irrigation development programme was signed in Rome on the 13th day of June 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 17th day of January, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Programme Financing Agreement for Participatory Small – Scale Irrigation Development Programme Ratification Proclamation No.563/2008".

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በሮም የተፈረመው የብድር ቁጥር 719-ET እና የእርዳታ ቁጥር DSF-004-ET ስምምነት ጸድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፫ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር /አሥራ ሦስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ.ህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Programme Financing Agreement Loan No. 719-ET and Grant No. DSF-004-ET signed in Rome on the 13th day of June 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 13,300,000 SDR (thirteen million three hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the financing Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 5th day of February, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**